# የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስትር ማን ነው?

ምሕረት ዘገዬ

እኔን መሰሉ የዋህ ሰው ግልጽ ጥያቄ በመጠየቅ የራሱንና የሌሎች ሰዎችን ጊዜ በከንቱ ያባክናል፡፡ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ለዜጎች ቀርቶ ለሣር ቅጠሉ በማያሻማ ሁኔታ ግልጥ ሆኖ ሣለ ይህን ጥያቄ መጠየቅ በርግጥም ሞኝነት ነው፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሀገራችን ኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ አህመድ ይመስለኝ ነበር፡፡ በቅርብ በተላለፈ የኤል ቲቪ አንድ የቃለ መጠይቅ ፕሮግራም መሠረት ግን ተሳስቼ እንደነበር ተረዳሁ፡፡ እናም በዚያ የጃዋር መሀመድና የቤተልሄም ታፈሰ የቃለ መጠይቅ ዝግጅት መገንዘብ የቻልኩት አቢይ አህመድ የጃዋር አሽከርና ጉዳይ አስፈጻሚ እንጂ ምንም ዓይነት እዚህ ግባ የሚባል ሥልጣን የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ሲጀመር አቢይ ለሚጠየቀው የጥፋትና ውድመት ጥያቄ ሁሉ መልሱ “አልሰማሁም፤ አላወቅሁም፤ አጣራለሁ…” እንጂ ኃላፊነት ሲወስድም ሆነ በሥሩ የሚገኙ ባለሥልጣናቱን ሲቆጣጠር አይታይም፡፡ ደግሞም እርሱ የተመሳጠረበት ይሁንም አይሁንም ብቻ አንድ ችግር ሊፈጠር ሲል ወደ ውጭ ሀገር ሹልክ የሚልበትና አንድ ሚሊዮን ሰው በሀገር ውስጥ አፈናቅሎ መቶ እስረኞችን ከውጭ ይዞ የሚመጣበት በዓይነቱ አዲስ የሆነ የማፍዘዣ ሥልት አለው፡፡ ይህ እጅግ ይገርመኛል፡፡ ልዩ አፍዝ አደንግዝ ነው፡፡ ይህ የአቢይ በሀገር ጉዳይ ባይተዋር የመሆን ነገር በራሱ የሚያሳየን ኢትዮጵያ ከዶክተር አቢይ ቁጥጥር መውጣቷንና እርሱ ጠ/ሚኒስትር መባሉ ለላንቲካ መሆኑን ነው፡፡

በበቀደሙ ቃለ መጠየቅ ጃዋር ከጠ/ሚኒስትርነትም ባለፈ የፈጣሪን ቦታ የተካ ያህል የሚሰማው ይመስለኛል፡፡ ቢያንስ የኛ የኢትዮጵያውያን ፈጣሪ (አላህም እንበለው እግዚአብሔር ወይም ዋቃ) እርሱ የሆነ ያህል እንደሚሰማው መገመት አላቃተኝም፡፡ ያለው የራስ መተማመንና የአድራጊ ፈጣሪነት ስሜት እጅግ የሚገርም ነው፡፡ ሀገራችን በሥውር ኃይሎች እየተገዛች እስከመቼ እንደምትቆይ አንድዬ ይወቅ፡፡

“አዎ፣ በዚህ ጉዳይም በጆሯቸው ሹክ ብለናቸዋል፤ ግን አልሰሙንም፡፡ ባለመስማታቸውም የሚደርስባቸውን ያውቃሉ፡፡ … ስለዚህም ጉዳይ ከጀርባ ሆነን ነግረናቸዋል፡፡ … ስለምትይውም ነገር አስጠንቅቀናቸዋል፡፡… የሲዳማን ነገር ተይው ያለቀለት ነው፡፡… ፈተናውን አሰርቀን ለሁሉም ክልሎች የበተንነው እኛ ነበርን … ለኦሮምያ ብቻ ማድረግም እንችል ነበር፡፡… ትምህርት ሚኒስቴር ብልሹ ነው፡፡ ደኢህዴን የሞተ ነው፡፡ … ስለሱም ጉዳይ ማስጠንቀቂያ ልከንላቸዋል፡፡ … ዝም ያልናቸው የትም እንደማይደርሱ ስለምናውቅ ነው፡፡”

ንጉሠ ነገሥት ወጠቅላይ ሚኒስትር ዘኢትዮጵያ ወኦሮምያ፣ ፊልድ ማርሻል ሃጂ ወፓትርያርክ ዘምድረ ሀበሻ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም … አቤቶሁን ጃዋር መሀመድ እንደዚያ ሊንቀባረር የቻለው በጌታዋ የተማመነችዋን በግ ሆኖ እንጂ አንድ “አክቲቪስት ነኝ” ባይ በምን ሥልጣንና ችሎታው እንዲያ እንደሚዘባነን ለማንም ግልጽ አይደለም - የነአልሲሲ ጠብደል ጉርሻ እስከዚህን ማጥገቡና የልብ ልብ መስጠቱ የሚደንቅ ነው፡፡ የሆኖ ሆኖ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ይህ ውሉደ አጋንንት ቆሻሻ ሰው እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡

ቀጣዮቹን ፎቶዎች እየፈታታችሁ ግጠሟቸው፡፡ ብዙ ትረዳላችሁ፡፡





ሦስቱ በሚታዩበት የመጀመሪያው ፎቶ አቢይ የገባው አቶ ለማን ግን ያልገባው ነገር እንዳለና ያንን ነገር ጃዋር እያስረዳው እንደሆነ እንረዳለን፡፡ አቢይም ለራሱ የገባው ነገር ለማም እንዲገባው የፈለገ ይመስላል፡፡ እነዚህ ሦስት ሰዎች ምን እየተመሳጠሩ እንደሆነ በፎቶው ባይገባንም በተግባር ግን አሁን የተዘፈቅንበት ችግር እየገለጠልን ይገኛል፡፡ የነዚህን ሰዎች ፀረ ኢትዮጵያዊነት ለመገንዘብ  ጤናማ ሰው

መሆንን ብቻ ይጠይቃል፡፡ ማንም አንፋሽ አከንፋሽና የሥልጣንና የፍርፋሪ ተስፈኛ እስኪነግረን አንጠብቅም፡፡ ዘመን ሲያልቅ ብዙ ጉድ ይወጣል፡፡ አሁን አሁን ሽሉም ገፍቷል፤ ቂጣውም ጠፍቷል፡፡ በየሚዲያው የተሰገሰገው ሆዳምና አድርባይ ሁሉ እየለየለት ስለመጣ ታሪካዊው ዕንቆቆና መተሬ ሥራውን በሚገባ እየሠራ ነው፡፡ ወደፊትና በቅርቡ ደግሞ ቋንቋ ከናካቴው የሚደበቅበትና ተግባር ብቻውን የሚናገርበት ጊዜ መምጠቱ አይቀርም፡፡ ቋንቋ በብዙ ነገሮች ውሱንነት አለበት፡፡ እውነትን ለማውጣት የመጥቀሙን ያህል ለመዋሸትና ለመቅጠፍም ይውላል፡፡

ሁለተኛው ፎቶ ላይ የሚታየው የአቢይ ምስል የልጁን - የአቢይን - ትክክለኛ ተፈጥሮ ይገልጻል፡፡ አስመሳዮችና የትያትር ሰዎች እንደዚህ ናቸው፡፡ ይህን ፎቶ ያነሳውና ያሰራጨው ሰው ልጅ ይውጣለት፡፡ ሾካኮችና ሞጥሟጣ አጭቤዎች በሚነሱዋቸው ፎቶግራፎችም በሚገባ ይታወቃሉ፡፡ የለማን ገርነትና ጨዋ ባሕርይ ግን ከፎቶው መገመት ይቻላል፡፡ ለማ ለዓላማው ሲል ከዘረኞቹ ጋር ቢዶልትም ተፈጥሮው ግን ቀና መሆኑን ፎቶዎቹ በግልጽ ይጠቁማሉ፡፡ወርቅነህ ሞኝ ቢጤ ነው ለጊዜው እንተወው፡፡ ማኪያቬሊ(ጃዋር) ግን ያለውን የእባብና የሸለምጥማጥ ጠባይ ከአኳኋኑ በሚገባ መረዳት ይቻላል፡፡ ለማንኛውም ድግሱ ተደግሷል፡፡ ጥሪውም ለሁሉም ተላልፏል፡፡ ብዛታቸው ሰማንያ ሰባት የሚደርሱ ፈረሶችን የሚያስጋልበው ድንኳኑና ዳሱም ተጥሏል፡፡ የሚቀረው ብፌውን የሚያስነሳው የፊሽካው መነፋት ብቻ ነው፡፡ በየአቅጣጫው ቀዳዳ እየተፈለገ ሀገር እንደ ዶሮ የምትበለትበት የቅርጫ ሥርዓቱ ተዘርግቶ አሁን በወረቀትና በሚዲያ ላይ ነገ ደግሞ ከ... ተጀምሮ መሀል ... በሚጠናቀቅ የጦርነት ዐውድማ የሀገራችን መፃዒ ዕድል ሊበየን ዝግጅቱ ሁሉ በየፊናው ተጠናቋል፡፡ ሦርያና ሩዋንዳም ጓዛቸውን ጠቅልለው የኢትዮጵያን ድምበር በመሻገር አዲስ አበባ ላይ መሽገዋል፡፡ ዕድሜ ለነጃዋርና እነሱን ለላኩ የግብጽና የምዕራቡ ኃያላን ሀገራት ድግሱ ይህ ቀረሽ በማይባልበት ሁኔታ ተደግሶ እንግዶቹን እየጠበቀ ነው፡፡ ሁሉም ቢላዎውን ስሎ ቁርጡን ሊበላ አሰፍስፏል፡፡ መልካም ዕልቂት ከወዲሁ፡፡ ከአድማስ ማዶ ካልተገናኘን አሁኑኑ ቻው፡፡

(በውጭ የምትኖሩ ዜጎች ላልተወሰነ ጊዜ በያላችሁበት ብትቆዩ መልካም ነው፡፡ ሃይማኖት ያላችሁ በየሃይማኖታችሁ ተግታችሁ ጸልዩ፡፡ ክፉ ዘመን ማለፉ ባይቀርም ጉዳቱ ችላ ሊባል የሚገባው አይደለምና ሀገራችንን በጥሞና እናስባት፡፡ ዶፉን እንዲያቀልልን በሱባኤና በምህላ ፈጣሪን እንለምነው፡፡ ዕድል ብርቂዎቹ አነጎችና አህዲዶች ከሀገራችን መሠሪ ጠላቶች ጋር በግልጽም በኅቡዕም በመመሳጠር ሀገራችንን በየቀኑ በሚባል ደረጃ ወደ ስቅለቷ እያዳፏት ነው፡፡ የትንሣኤዋን እውን መሆን ማንም ባያስቀረውም ሰሙነ ህማማቷና ስቃይዋ እንዲቀልላት ለሀገራችን ሁላችንም በየእምነታችን እንጸልይ፡፡ ያም የሚሆነው ዛሬ እንጂ ነገ አይደለም - ነገ ዕድሉ አይኖረንምና፡፡ ...)